**ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል**

**26 ኛ ሳምንት**

**ሆሣዕና**

**ዓላማ**

❖ ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን መማር

**የሚጠና ጥቅስ**

❖ *«ለሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ ምሥጋናን አዘጋጀሀ»* ማቴ 21÷16

**ምንባብ**

❖ ማቴ.21÷1-16

**መግቢያ**

❖ ሆሣዕና መድኃኒት ማለት ሲሆን የዛሬው ትምህርታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞቱና ትንሣኤው በፊት ባለው እሁድ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱን ማየት ሲሆን፤ በክብር መግባት ስንልም ሞትን በሞቱ እና ትንሣኤው አጥፍቶ፣ለሕያዋንና ለሙታን ድኅነትን ያውጅ ዘንድ ስለገባ ነው፡፡ሕዝቡ የያዘው የዘንባባ ዝንጠፊም የክብሩ መገለጫ እና ምሳሌ ነበር፡፡

❖ በዘሌዋ. 23÷40 እንደተገለጠውም ዘንባባ የክብርና ምሥጋና ምሳሌ ነበር፡፡

❖ ሕጻናትና አዋቂዎች ዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው ደስታቸውንናክብራቸውን ለክርስቶስ የገለጡት ከዚህ ተነስተው ነው፡፡

**ትምህርቱ**

❖ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአይሁድ በዓለ ፋሲካ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፤በኢየሩሳሌም በዓል ለማክበር የተሰበሰበው ሕዝብ አልዓዛርን ከሞት ማስነሳቱን ስለሰሙ ብዙ ሕዝብ ሊቀበለው ወጣ፡፡

❖ ወደ ኢየሩሳሌም ከመውጣቱ በፊትም ሁለት ደቀመዛሙርቱን *« በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ÷ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ፡፡ ማንም እንዳች ቢላችሁ፦ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል፡፡»* ማቴ.21÷2-3

❖ ደቀመዛሙርቱ እንደታዘዙት ሄደው አገኙ፡፡ፈትተው ሲመጡም የአህዮቹ ጌታ ጠየቃቸው ጌታ መፈለጉን ሲነግሩትም ሰደዳቸው

❖ ጌታችን በውርንጫይቱ (ወጣትዋ አህያ ላይ) ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፡፡ሕዝቡ ልብሳቸውን የዘንባባ ዝንጣፊና የሌሎች ዛፎች ጫፍ እየቆረጡ መንገድ ላይ በማንጠፍ ተቀበሉት፡፡

❖ ብዙ ሕጻናትም *«ሆሣዕና በአርያም በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፡፡»* እያሉ ዘመሩ፡፡

❖ ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ጌታችንና መድኃኒታችን የመረጣቸው የሆነውን በመጀመሪያ አላስተዋሉም ነበር፡፡በኋላ ግን ነቢያት ቀድመው ተንብየው እንደነበርና ያም መፈጸሙን አስተዋሉ፡፡

❖ ነቢይናመዝሙረኛው ዳዊት*«ለሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ ምሥጋናን ለራስን አዘጋጅሀ»*መዝ.8÷2 ሲል ቀድሞ ተንብዬ ነበር፡፡

❖ በነቢዩ ዘካርያስም *«ለጽዮን ልጅ፦እነሆ÷ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉኣት»* ትን.ዘካር.9÷9 ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ፡፡

❖ ነገር ግን የአይሁድናየካህናት አለቆች ቀንተው *«እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን?»* በማለት ዝም ለማሰኘት ሞከሩ፡፡ጌታችንም*«እሰማለሁ»* ብሎ በነቢያት የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን አስታወሳቸው፡፡

**ማጠቃሊያ**

❖ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጨረሻ ጊዜ የገባበት ሰንበት ከመስቀሉ በፊት ያለችው ሰንበት ናት፡፡

❖ ብዙ ሕዝብ ሲከተለው ሳላዩ ቀኑ፡፡ይኽ ቅናትም ሊያድናቸው የመጣውን ለመስቀል አሳልፎ ለመስጠት አበቃቸው፡፡

❖ የካህናት አለቆችና ፈረሳውንያን ምንም እንኳ መጻሕፍት አዋቂዎች ቢሆኑና ስለክርስቶስ የተባለውን ቢውቁም ለክብራቸው ሲሉና ቅንዓት ዓይናቸውን አሳውሮት ጌታችንን መቀበልና ማመን አልቻሉም ነበር፡፡

❖ በዚህም የሐሰት ክስ በክስቶስ ላይ በማቅረብ አርብ እለት ሰቀሉት፡፡ጌታችን ግን ክሳቸውንና ተንኮላቸውን አውቆ በሞቱና በትንሣኤው ሞትን ይሽር ዘንድ ለሞት ራሱን አሳልፎ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ፡፡

❖ ከሆሣዕና እሁድ በኋላ ያለው ሳምንት « ስሙነ ሕማማት » የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራና ሥቅለት መታሰቢያ ቀናት ናቸው፡፡

**ጥያቄዎችና ልምምዶች**

1. የጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም መግባት ለምን *« የክብር »*ተባለ? ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ሕዝቡ እንዴት ተቀበለው?
2. የዘንባባ ዝንጣፊ የምን ምሳሌ ነበር? ክርስቶስ እንዴት ወደ እየሩሳሌም ገባ?
3. የአይሁድ ሊቃውንትና መሪዎች በጌታችን ለምን ቀኑ? በቅናታቸውስ ምን ሠሩ? ከሆሣዕና በኋላ ያለው ሳምንት ምን ይባላል?
4. ስለ ሆሣዕና ትንቢት የተነገረባቸው መጻሕፍት የትኞቹ ናቸው፡፡

**መዝሙር**

ሆሣዕና በአርያም

እያሉ ዘመሩ ሕፃናት በኢየሩሳሌም

**ይቆየን፡፡**